ኢ.ፌ.ዴ.ሪቤ
ዚሐረሪ ኡመት ሑስኒ ሑኩማ
ረኢስ መክተባ ጋር
F.D.R.I.tti
Waajjira Pireezdaanti
Mootummaa Naannoo Ummata Hararii

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ
የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት
ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
F.D.R.E
The Harari People Regional State
Office of the President

ኒምራ (ቁጥር)
Lakk (Ref. No) 10-3/4/14/2007
አያም (ቀን)
Guyyaa (Date) 30 የካቲት 2007

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር

ለዲያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

<u>አዲስ አበባ</u>

**<u>ጉዳዩ :- የፀደቀ መመሪያ መላክን ይመለከታል ::</u>**

የሀረሪ ህ/ብ/ክ/መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት በቀን 19/06/07 ተሰብስቦ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልድ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤቶች ህብረት ሥራ ማህበር ፕሮግራም የቤት ፈላጊዎች የምዝገባ ማስፀሚያ መመሪያ ላይ በመወያየት መመሪያው ያፀደቀው ሲሆን የፀደቀውን መመሪያ .... ገፅ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አያይዘን መላካችንን እንገልፃለን ::

ከሰላምታ ጋር

ይማጅ ከማል
ካቢኔ ሐጃ ዋ ሻዐቢ መትሐዳሮቲ
መክተባ ጋር ኤ/መስኡል
Yimaaj Kamaal
He/Hoogganna Wajjira Dhimma
Kabiineefi Bulchinsa Ummataa

<u>ግልባጭ</u>

- ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት
- ካቢኔ ጉዳይና ህ/አስ/ጽ/ቤት
- ለዲያስፖራ እና ውጭ ግንኙነት ስራ ሒዳት

<u>ሀረር</u>

መልሱን በሚጽፉበት ጊዜ የእኛን ደብዳቤ ቁጥር ይጥቀሱ
Please quote our Ref. No when replying
ኢትዮጵያ - Ethiopia
E-mail:- harpreof@ethionet.et

ፋክሲ 0256-660666
Telefax 0256-66 1799

0256-666699
0256-660452
272

# በሐረሪ ሕ/ክልላዊ መንግስት
# ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ

በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን

በመኖሪያ ቤቶች ኅብረት ሥራ ማኅበር ኘሮግራም የቤት ፈላጊዎች የምዝገባ

ማስፈጸሚያ መመሪያ

የሐረሪ ህዝብ ቤሌራዊ ክልላዊ መንግስት
የሪከርድና ማህደር አገልግሎት ክፍል
ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት

የካቲት/2007 ዓ.ም.

ሐረር

## ማውጫ


| ተ.ቁ | ርዕስ | ገጽ |
|---|---|---|
| | መግቢያ | 1 |
| | **ክፍል አንድ** **ጠቅላላ** | |
| 1. | አጭር ርዕስ | 2 |
| 2. | ትርጓሜ | 2 |
| 3. | የተፈጻሚነት ወሰን | 3 |
| 4. | የማስፈጸሚያ መመሪያው ዓላማ | 3 |
| 5. | መርሆዎች | 4 |
| | **ክፍል ሁለት** **የምዝገባ መስፈርት** | |
| 6. | በግል የመኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች | 4 |
| 7. | በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁ ቤት ፈላጊዎች | 5 |
| 8. | በኢ.ፌዲ.ሪ ሚሲዮኖች ተመድበው የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች | 5 |
| | **ክፍል ሦስት** **የሂሳብ አከፋፈት፣ የቤቶች ዓይነትና የምዝገባ ዋጋ** | |
| 9. | የባንክ ሂሳብ አከፋፈት | 6 |
| 10. | የሚገነቡ ቤቶች ዓይነት፣ስፋት እና የቤቶች የምዝገባ ዋጋ | 7 |
| | **ክፍል አራት** **ተግባርና ኃላፊነቶች** | |
| 11. | የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ | 8 |
| 12. | የሐረሪ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት | 9 |
| 13. | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | 11 |
| 14. | ማህበራት ማደራጃና ሠራተኛና መህበራዊ ጉ/ጽ/ቤት | 11 |
| 15. | የቤቶች ልማት ኢንተርኘራይዝ/ተቋም | 12 |
| | **ክፍል አምስት** **ልዩ ልዩ ጉዳዮች** | |
| 16. | ስለ ውክልና | 12 |
| 17. | የምዝገባ ጊዜ | 12 |
| 18. | የሂሳብ እንቅስቃሴና የገንዘብ ዝውውር ሁኔታ | 13 |
| 19. | የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ክትትል | 13 |
| 20. | የመኖሪያ ቤት ርክክብና ቅድሚያ አወሳሰን | 13 |
| 21. | ከፕሮግራሙ ስለመሰረዝ | 14 |
| 22. | ቁጠባው ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ | 14 |
| 23. | ክልከላ | 14 |
| 24. | ቅጣት | 14 |
| 25. | የማስፈጸሚያ መመሪያውን ስለማሻሻል | 14 |
| | አባሪ አንድ | 15 |
| | አባሪ ሁለት | 17 |
| | አባሪ ሶስት | 19 |

## መግቢያ

የሐረሪ ክልል መንግስት በተለያዩ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን (ዳያስፖራ) በትውልድ ሀገራቸው ሁሉን አቀፍ የልማት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል የዳያስፖራ ፖሊሲ ቀርፆ ተግባራዊ እንቅስቃሴ እያደረገ ይገኛል፡፡ ዳያስፖራው በግልና በማህበር ተደራጅቶ የቁጠባ ሥርዓትን መሠረት ያደረገ የመኖሪያ ቤት ስለሚያገኙበት ሁኔታ በጥናት ላይ የተመሠረተ አሠራር እንደሚዘረጋ በተደነገገው እና በሃገር አቀፉ የከተማ ቤት አቅርቦት ስትራቴጂ ማዕቀፍ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ቀደም ብሎ በክልሉ ዳስፖራውን ከሀገሩ ጋር ለማስተሳሰር በአይነቱ ልዩ በሆነ ሁኔታ የክልሉን ኪነ-ህንጻና ባህላዊ የህንጻ ጥበብን ገፅታ የተላበሱ ዘመናዊ ቤቶችን ባጣመረ መልክ የሚገነቡ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ፕሮጀክት እየተካሄደ ያለ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህም የግንባታ ፕሮጀክቱ በህብረተሠቡ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ቁጠባን ማዕከል ያደረገ ከወለድ ንክኪ ነፃ የሆነና በሪቮልቪንግ ፈንድ ሲስተም አማካኝነት በተመጣጣኝ ዋጋ ቤት ሰርቶ ለማስረከብ የተጀመረ ፕሮጀክት ነው፡፡

በዚህ ፕሮጀክት ከፍተኛ የሆነ የውጭ ምንዛሪ ከሐረሪ ተወላጆችና ከሐረር አፍቃሪዎች ወደ ሀገራችን ለማስገባትና የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ቴክኖሎጂ ወደዚህ ፕሮጀክት በማሸጋገር የጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራትን ተጠቃሚነት በማረጋገጥና ዘላቂ የሆነ የስራ ዕድል ለመፍጠር በማሠብ በተከታታይ ዓመታት ከ200 በላይ ቤቶችን ለመገንባት ታቅዶ ሙሉ በሙሉ ግንባታው ተጀምሮ ግማሹ ግንባታው ተጠናቆ በዕጣ ለህብረተሠቡ የተላለፉ ሲሆን ቀሪዎች ግንባታዎችም እየተጠናቀቁ ይገኛሉ፡፡ይህ ቀድሞ የተጀመሩ ልምዶችና ተሞክሮዎችን በማጎልበት እና አሁን የወጣውን የዲያስፖራ መኖሪያ ቤት ማስፈፀሚያ ሞዴል መመሪያን መሠረት በማድረግ የክልሉ ተጨባጭ ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ መመሪያ እንደሚከተለው ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

- በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበራት በመደራጀት በመኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆን የሚችሉበት ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በውጭ ምንዛሪ ቆጥበው በቤት ልማት ፕሮግራሙ ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የቤት ባለቤት እንዲሆኑና ከእናት ሃገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር ከማጠናከር ጎን ለጎን ለኢኮኖሚው አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ የሚረዳ ግልጽ የምዝገባ፣ የአደረጃጀትና የቁጠባ ስርዓቱን የሚያሳይ ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣
- የሐረሪ ከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ከክልሉ ዲያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እና በክልሉ በማህበራት ማደራጃ የሚመለከታቸው አካላት ጋር የተቀናጀና የተናበበ የአሰራር ስርዓት በመፍጠር በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር፣ የቤት ልማት ፕሮግራም ተጠቃሚ ለመሆን የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በሐረሪ ክልል ሲካሄድ የምዝገባ ስርዓቱ ተቀራራቢነት፣ ግልጽነትና ፍትሃዊነት ባለው መልኩ ለማካሄድ እንዲቻል፣

የሐረሪ ህ/ክ/መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት፣ተጠሪነት ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን የወጣ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 47/1997 አንቀጽ 32 (2) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ዝርዝር የማስፈጸሚያ መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ የማስፈጸሚያ መመሪያ "በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የምዝገባ ማስፈጸሚያ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

1) "የኢትዮጵያ ዳያስፖራ" ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ማለት ነው።

2) "ሀዋላ" ማለት በውጭም ሆነ በሀገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች ወይም የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች አማካኝነት ገንዘብ የማዘዋወሪያ ዘዴ ነው።

3) "ዲፕሎማቲክ ፓውች" ማለት በቪየና ኮንቬንሽን መሰረት ለአንድ ሚሲዮን ኦፊሴላዊ ሥራ ብቻ እንዲያገለግሉ የተፈቀዱ ሠነዶች መያዣና መላላኪያ ከረጢት ነው፣

4) "ሚሲዮን" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት በውጭ ሀገር ያቋቋመው ወይም የሚያቋቁመው ኤምባሲ ወይም ቋሚ መልዕክተኛ ጽ/ቤት ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ነው፣

5) "ነባር የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር" ማለት በውጭ ሀገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያውያን እንዲሁም ተመላሽ ዳያስፖራ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅቶ በዝግ ሂሳብ ገንዘብ ያስቀመጠ፣ በማህበራት ማደራጃ ተቋም የምዝገባ ሠርቲፊኬት ያለውና እስካሁን ድረስ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ቦታ ያልተረከበ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ነው፡

6) "አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር" ማለት በማህበር በመደራጀት ባህላዊና ዘመናዊ ታውን ሃውስ እና አፓርትመንት ቤቶችን ለመገንባት የሚፈልጉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ለመመዝገብ ይህ የምዝገባ ማስፈጸሚያ መመሪያ [redacted] ጸድቆ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በአዲስ መልክ የሚቋቋም የቤት ህብረት ስራ ማህበር ማለት ነው።

7) "በግል ተመዝጋቢ" ማለት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በአፓርትመንት ፣ በታውን ሃውስ ወይም በባህላዊ ቤቶች በተናጠል ተመዝግቦ በጋራ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ነው።

8) "የውክልና ማስረጃ" ማለት በህግ የተደነገገ ሥርዓትን ተከትሎ በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል /ውልና ማስረጃ - Notary Public/ እና ሚሲዮን በአካል ቀርቦ የተሰጠ እና በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በውልና ማስረጃ መሥሪያ ቤት የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ ነው ።

9) "ንግድ ባንክ" ማለት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ማለት ነው፣

10) "ኤጀንሲ" ማለት በክልሉ የመኖሪያ ቤቶችንና መንግስት ኮንስትራክሽኖችን ለማስገንባት የተቋቋመ የመንግስት ተቋም ነው።

11) "ኢንተርፕራይዝ" ማለት የቁጠባ ቤቶችን ለመገንባት የሚቋቋመው የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም በክልሉ መንግስት ወደፊት የሚቋቋም የቤት ልማት ኢንተርፕራይዝ ነው።

12) "ዲፕሎማት" ማለት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከሌሎች መንግታስዊ መሥሪያ ቤቶች በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሚሲዮኖች በውጭ ግንኙነት መስክ ተመድቦ የሚያገለግል ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ ማለት ነው፣

13) “ሎካል ሠራተኛ” ማለት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ በሌሎች መንግስታዊ መሥሪያ ቤቶች እና ኢፌዴሪ ሚሲዮን ተቀጥሮ በኢፌዴሪ ሚሲዮን ተመድቦ እያገለገለ የሚገኝ ኢትዮጵያዊ ሠራተኛ (non-diplomatic staff) ነው፡፡

14) "ተመላሽ ዳያስፖራ" ማለት ለተለያዩ ምክንያቶች ወደ ሀገር ውስጥ ከተመለሱ ከሁለት ዓመት በላይ የቆዩ እና በተለያዩ ስራዎች ተሰማርተው የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ማለት ነው፡፡

15) “የማኅበራት ማደራጃ” ማለት የክልሉ ማህበራት ማደራጃና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ነው፡፡

16) “ታውን ሀውስ” ማለት ጂ+1 ወይም ጂ+2 ወለል ያለው ራሱን የቻለ መጠነኛ ግቢ እና መግቢያ ያለው የመኖሪያ ህንፃ ሲሆን ከአጐራባች መኖሪያ ቤቶች ጋር በግድግዳ የተያያዘ መኖሪያ ቤት ማለት ነው፡፡

17) “የባህል ቤት” ማለት የሐረሪ ኪነ ህንፃ ጥበብ የተላበሰ እና የዘመናዊ ቤት ገጽታ ያለው ጂ+1 ወይም ጂ+2 ወለል ያለው ራሱን የቻለ መጠነኛ ግቢ እና መግቢያ ያለው የመኖሪያ ህንፃ ሲሆን ከአጐራባች መኖሪያ ቤቶች ጋር በግድግዳ የተያያዘ መኖሪያ ቤት ማለት ነው፡፡

18) “አፓርትመንት” ማለት ጂ+4 እና ከዚያ በላይ ወለል ያላቸው በመሬት አጠቃቀም ፕላኑ መሠረት የሚገነቡ የጋራ መኖሪያ ሕንፃዎች ሆነው በጋራ የመኖሪያ ቤት ህግ መሠረት በግል ባለቤትነት የሚያዝ የተሟላ የመኖሪያ ቤት ማለት ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ በክልሉ መንግስት አስተባባሪነትና ድጋፍ ከሚገነቡት የዳያስፖራ ቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ያልሆኑ በግል ተመዝግበው በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር የሚደራጁ እና በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው ባህላዊ፣አፓርትመንትና ታውን ሃውስ ለመገንባት የሚፈልጉ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ በኢፌዴሪ ሚሲዮኖች ተመድበው/ተቀጥረው በሥራ ላይ የሚገኙ ዲፕሎማቶች እና ሎካል ሰራተኞች እንዲሁም ተመላሽ ዳያስፖራ አባላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፣

2) መመሪያው በክልሉ ካቢኔ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ በክልሉ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በዚሁ መሠረት በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በትውልድ ክልላቸው ለመመዝገብ እንዲችሉ በጸደቀው መመሪያ መሠረት ምዝገባውና የቦታ ዝግጅቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

3) ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ቀን በፊት በቤቶች ልማትና መንግስት ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ በዚህ ፕሮግራም ተመዝግበው የከፈሉ ቤት ባለቤቶች በቀድሞው አሠራር ተስተናግደው ቤታቸውን እንዲረከቡ ይደረጋል እንዲሁም ከዚህ በኋላ ቀድሞ በተለምዶ ይሠራባቸው የነበሩ የዳያስፖራ ቤቶች ምዝገባ አሠራሮች በዚህ መመሪያ ተተክቷል፡፡

4) በ2000 ዓ.ም ሚሌኒየም ለዲያስፖራዎች ጊዜያዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ተሠጥቷቸው በቦታ ለውጥ እስከአሁን መሬት ያላገኙት ላይ መመሪያው ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 4. የማስፈጸሚያ መመሪያው ዓላማ

1) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በቤት ልማት ፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን ለምዝገባ መስፈርት የሚያስፈልገውን ዝርዝር የአሰራር ሂደት ግልጽ ለማድረግ፣

2) በምዝገባ ሂደት የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ግልጽ የአሰራር ስርዓት ለመዘርጋትና ተግባርና ኃላፊነታቸውን አውቀው መመሪያውን እንዲያስፈጽሙ ለማድረግ፣

5. መርሆዎች

1) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚካሄዱ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ለሀገራቸው ልማት አስተዋጽዖ እንዲያደርጉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ፡፡

2) ግልጽ እና ፈጣን የምዝገባ፣ የቁጠባና የአደረጃጀት ስርዓት በመከተል መረጃዎች ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

3) ባለድርሻ አካላት በተቀናጀና አሳታፊ በሆነ መልኩ ለጋራ ዓላማ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና ተመላሽ ዳያስፖራን ለመደገፍ መንግስት እያደረገ ያለውን ጥረት እንዲያግዙ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የምዝገባ መስፈርት

### 6. በግል የመኖሪያ ቤት ተመዝጋቢዎች

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በግል ተመዝግበው በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተደራጅተው በታውን ሀውስ፣ባህል ቤቶች እና አፓርትመንት ቤት ለመገንባት ፍላጎት ያላቸው የሚከተሉትን በማሟላት ምዝገባ ማከናወን ይችላሉ፡፡

1) የጸና የፓስፖርት ቅጂ እና የሚኖሩበት አገር የጸና የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኢትዮጵያ(ክልሉን የሚወክል) ኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

2) የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆኑ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

3) የጋብቻ ማስረጃ ዋናውንና ቅጅውን፣

4) ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፣

5) ለዚሁ ጉዳይ የተዘጋጀ የምዝገባ ቅጽና ውል ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣

6) ተመዝጋቢዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፣

7) በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት ሙሉ ክፍያ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በሚከፈተው የብር ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፣

8) በመረጡት የቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ክፍያ በምዝገባ ወቅት በሚኖሩበት አገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በኩል የባንክ ሂሳብ በመክፈት የሚያስቀምጥና መሬት ተዘጋጅቶ የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበሩ ሲረከብ የቀሪውን 50 በመቶ ሙሉ በሙሉ በመክፈል የግንባታ ፍቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ እና በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በሚከፈተው የብር ሂሳብ ገቢ ያደረጉበትን የደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ፣

9) ግለሰቡ እንደተደራጀ የሚቆጠረው የግንባታውን ወጪ 50 ፐርሰንት ክፍያ ፈጽሞ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣

10) ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በክልሉ ውስጥ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣

## 7. በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የተደራጁ ቤት ፈላጊዎች

በዚህ ፕሮግራም መሳተፍ የሚፈልጉ ማህበራት፡-

1) ከዚህ በፊት በራሱም ሆነ በትዳር ጓደኛው ስም የመኖሪያ ቤትም ሆነ የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ በክልሉ ውስጥ የሌለው ወይም ኖሮት ለሶስተኛ ወገን ያላስተላለፈ፣

2) በክልሉ መንግስት አስቀድሞ በተዘረጉት የዲያስፖራ ቤት ልማት ፕሮግራም ላይ ተጠቃሚ ያልሆነ ወይም ለመጠቀም ያልተመዘገበ ወይም ተመዝግቦም ከሆነ ምዝገባውን መሠረዙን ወይም መተውን ግዴታ መግባት የሚችል፣

3) አንድ ማህበር በህጋዊ መንገድ በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ለመመዝገብ የሚችለው ሁሉም የማህበሩ አባላት የተገመተውን የግንባታ ወጪ 50 በመቶ መክፈል ሲችሉ ብቻ ነው፣

4) ማህበሩ እንደተመሠረተ የሚቆጠረው የተገመተውን የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ክፍያ ፈጽሞ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፣

5) የነባር ማህበራትን አመዘጋገብ በተመለከተ የክልሉ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና ከሚመለከታቸው የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት ጋር በጋራ ተስማምተው በሚያቀርቡት ዝርዝር ስምምነት መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፣

6) ሁሉም የህብረት ሥራ ማህበራት የራሳቸው መጠሪያ ሲኖራቸው በመጠሪያ ማህበራት ስር ያሉ አባላት በሙሉ የሚቀርብላቸውን ቅጽ 005 በራሳቸው ካልቻሉም በወኪላቸው አማካኝነት ሙሉ በሙሉ መሙላት ይገባቸዋል፣

7) የህብረት ስራ ማህበር አባላት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መንግስት በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት የጣት አሻራ ለመስጠት ፈቃደኛ መሆን ይገባቸዋል፣

8) በክልሉ ቤት ለማስራት የሚደራጁ የህብረት ስራ ማህበራት የቤቶች ኢንተርፕራይዝ/ተቋም ከሚያቀርበው ዲዛይን በተጨማሪ የራሳቸውን የግንባታ ዲዛይን በማዘጋጀት ማቅረብ የሚችሉ ሲሆን ዲዛይኑ እንደ አግባቡ ከተማ ልማት ቢሮ (የሚወክለው) አካል ሲያጸድቀው ተግባራዊ ይሆናል፣

9) በማህበር ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት ለመስራት ለሚፈልጉ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም ተመላሽ ዳያስፖራ አባላት ወደ ክልሉ እንደመጡ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ እንዲስተናገዱ ይደረጋል፣

10) ከላይ የተጠቀሱ በክልሉ የሚመዘገቡ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባው በዚህ ፕሮግራም መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

## 8. በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች

1) በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሚሲዮኖች የሚሰሩ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች በክልሉ በጸደቀው የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር የአደረጃጀት መመሪያ ከተመለከቱት የምዝገባ መስፈርቶች በተጨማሪ :-

    ሀ) የጸና የኢትዮጵያ ፓስፖርት ቅጂ እና

    ለ) ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሚሰጥ ማረጋገጫ ደብዳቤ

አሟልተው ምዝገባ ማከናወን ከፈለጉ በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታ ወጪውን 50 በመቶ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው በዳያስፖራው የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ተመዝግበው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሠው ሀብት ማኔጅመንት ዳ/ጄኔራል መላክ አለባቸው።

## ክፍል ሦስት

## የባንክ ሂሳብ አከፋፈት፣ የቤቶች ዓይነትና የምዝገባ ዋጋ

9. የባንክ ሂሳብ አከፋፈት

1) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለሁሉም የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትና በግል ተመዝጋቢዎች የሚያገለግል የባንክ ሂሳብ የመክፈት አገልግሎት ብቻ ይሰጣል፣

2) የሚመለከተው የህብረት ሥራ የማኅበራት ማደራጃ የጋራ አካውንት (pull account) በመክፈት ሁሉም ማኅበራት በእያንዳንዳቸው ሰብሲዲያሪ ሌጀር ተይዞላቸው ከምዝገባው በፊት ወደዚህ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡

3) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገቢ የተደረገውን የእያንዳንዱን ማኅበር የገንዘብ መጠን በተመለከተ ማረጋገጫ ለማኅበራት ማደራጃ፣ለክልሉ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ይልካል፣

4) ቤት ፈላጊ የዳያስፖራ አባላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ሥር የተገለጹትን ሳይጨምር እንዲገነባላቸው የፈለጉትን የቤት አይነት የክፍያ መጠን በውጭ ምንዛሪ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡

5) ተመዝጋቢዎች ክፍያ የሚፈጽሙበት ሃገሪቱ በምትገበይባቸው ገንዘቦች ብቻ ይሆናል፡፡

6) ተመዝጋቢዎቹ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የዳያስፖራ አካውንት ካላቸው ከዚህ ሂሳብ ወደ መኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሂሳብ እንዲዞርላቸው ማድረግ ይችላሉ፣

7) ነባር ማኅበራት ዝግ ሂሳባቸው በሌላ ባንክ ከሆነ ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማዞር አዲስ የባንክ ሂሳብ በብር መክፈት ይጠበቅባቸዋል፣

8) በውጭ ሀገር የሚኖሩ በግል ተመዝጋቢዎችና በማህበር የተደራጁ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የምዝገባና የባንክ ሂሳብ የመክፈት ሂደቱን ለማስፈጸም ማሟላት የሚጠበቅባቸው መሥፈርቶች

   ሀ) የጸና የፓስፖርት ቅጂ እና ከሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ

   ለ) የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆነ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ

   ሐ) ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ

   መ) ለዚህ ጉዳይ የተዘጋጀውን የምዝገባ ቅጽና ውል ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣

   ሠ) በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሪ በመላክ በአገር ውስጥ በሚከፈተው የብር አካውንት ገቢ ያደረጉበትን የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

9) በተለያየ ምክንያት ከግንባታ በኃላ በአካል በኢፌዲሪ ሚሲዮን ቀርበው መከታተል የማይችሉ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግል ተመዝጋቢና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የሚገነቡ መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የሚከተለውን አሟልተው መመዝገብ ይችላሉ፡፡

   ሀ) የወካይ የጸና የፓስፖርት ቅጂ እና ከሚኖሩበት አገር የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የኮሚኒቲ ማህበር አባልነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

   ለ) ወካይ እና ተወካይ የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆነ የወካይ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣

   ሐ) የወካዩ ሁለት ፓስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፣

መ) ተወካይ ወካዩን በተመለከተ የተሰጠው መረጃ ስህተት ከሆነ ለመጠየቅ የዝግጁነት ማረጋገጫ ማመልከቻ፣

10) በአገር ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የሙያ ሥራ ዘርፎች የተሰማሩና አገር ውስጥ ሁለት ዓመት እና ከዚያ በላይ እየኖሩ ያሉ ተመላሽ ተወላጅ ዳያስፖራ አባላት የሚከተሉትን ሲያሟሉ ብቻ በኢትዮጵያ ብር ከፍለው ሂሳብ መክፈት ይችላሉ፡፡

ሀ) ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የሆኑ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላትን በተመለከተ

1. የጸና ፓስፖርት ዋናውንና ቅጂውን፣
2. የውጭ ዜግነት ያለው ከሆነ የጸና የትውልድ ኢትዮጵያዊ መታወቂያ ካርድ ዋናውንና ቅጂውን፣
3. አገር ውስጥ ቢያንስ ሁለት ዓመትና ከዚያ በላይ መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከክልሉ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማቅረብ፣
4. በሀገር ውስጥ አለም አቀፍ ወይም አህጉራዊ ድርጅቶች፣ በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራና ወርሀዊ ክፍያው በኢትዮጵያ ብር እንደሆነና ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከክልሉ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማቅረብ የሚችል፣
5. በሀገር ውስጥ ሌላ የመተዳደሪያ ገቢ ካለው ይህንኑ የሚገልጽ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ለ) ኢትዮጵያዊያን የሆኑ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላትን በተመለከተ

1. የጸና ፓስፖርት ዋናውንና ቅጂውን
2. ከኖረበት አገር የጸና የመኖሪያ ፈቃድ ዋናውንና ቅጂውን
3. አገር ውስጥ ከሁለት ዓመት በላይ ያለመኖሩን/ሯን የሚያሳይ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን ወይም
4. በሀገር ውስጥ በአለም አቀፍ /አህጉራዊ ድርጅቶች፣ በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በግል ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራና ወርሀዊ ክፍያው በኢትዮጵያ ብር እንደሆነና ግብር ከፋይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከክልሉ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

11) በሃገር ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት የንግድና የሙያ የሥራ ዘርፎች የተሰማሩና ሃገር ውስጥ ከሁለት ዓመት በታች ለሆነ ጊዜ እየኖሩ ያሉ ኢትዮጵያዊ ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት እና ከ2 ዓመት በላይ በአገር ቤት የኖሩ ኢትዮጵያዊ የዳያስፖራ አባላት በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 10 ሀ እና ለ ሥር የተገለጹትን ሲያሟሉ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በብር ሂሳብ በመክፈት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## 10. የሚገነቡ ቤቶች ዓይነት፣ ስፋት እና የቤቶች ዋጋ

1) በውጭ ሃገር በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግል ተመዝጋቢና የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የሚገነቡት መኖሪያ ቤቶች አፓርትመንት፣ባህላዊ እና ታውን ሀውስ ሲሆኑ የቤቶቹ ስፋት እና ጠቅላላ ዋጋ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሀ) በአፓርትመንት (G+4 እና በላይ) አማራጭ**

1. ባለ 2 መኝታ የቤቱ ስፋት 74 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 424,390.00 ወይም (በካ.ሜ.ብር 5,735) ነው፡፡
2. ባለ 3 መኝታ የቤቱ ስፋት 100 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 573,500.00 ወይም (በካ.ሜ.ብር 5,735) ነው፡፡
3. ባለ 4 መኝታ የቤቱ ስፋት 136 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 779,960.00 ወይም (በካ.ሜ.ብር 5,735) ነው፡፡

ለ) በታውን ሀውስ (G+2) አማራጭ

1. ባለ 3 መኝታ የቤቱ ስፋት 114 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 693,120 ወይም (በካ.ሜ.ብር 6,080) ነው፡፡
2. ባለ 4 መኝታ የቤቱ ስፋት 150 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 912,000 ወይም (በካ.ሜ.ብር 6,080) ነው፡፡

ሐ) በታውን ሀውስ የክልሉን ባህላዊ ኪነ ህንጻ ጥበብ ያማከለ (G+2) አማራጭ

1.ባለ 6 መኝታ የቤቱ ስፋት 181.18 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 1,101,574 ወይም (በካ.ሜ.ብር 6,080) ነው፡፡

መ) በታውን ሀውስ የክልሉን ባህላዊ ኪነ ህንጻ ጥበብ ያማከለ (G+1) አማራጭ

1. ባለ 4 መኝታ የቤቱ ስፋት 129.63 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 788,150 ወይም (በካ.ሜ.ብር 6,080) ነው፡፡

2. ባለ 7 መኝታ የቤቱ ስፋት 247.55 ካ.ሜ. ሲሆን ዋጋው ብር 1,505,104 ወይም (በካ.ሜ.ብር 6,080) ነው፡፡

2) ከላይ የተጠቀሱት የግንባታ ዋጋዎች በአሁኑ ወቅት ያለውን የግንባታ ዋጋ የሚያሳዩ ሲሆኑ አሁን ባልታዩ አሳማኝ በሆኑ ምክንያቶኛ የዋጋ ልዩነት ሊኖር ይችላል፡፡
3) ከሁለት በላይ የሆኑ ማኅበራት (24 እና ከዚያ በላይ አባላት) በዩኒየን ተደራጅተው High rise ህንፃ በመሃል ከተማ መገንባት ከፈለጉ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲገነቡ የሚፈቀድላቸው ይሆናል፡፡
4) በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ምዝገባና አደረጃጀት በተለይ የማህበራት አባላት ብዛት፣ በቤት ዓይነት፣ በመኝታ ቤትና በህንጻ ከፍታ ተለይቶ የተቀመጠው ስታንዳርድ በዚህ መመሪያ አባሪ ሶስት ላይ ተያይዟል፡፡

## ክፍል አራት

## ተግባርና ኃላፊነቶች

### 11. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ

1) ለክልሉ ዲያስፖራ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበርና በግል ተመዝጋቢዎች የሚገነቡ አፓርትመንት እና ታውን ሀውስ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ የሚሳተፉ የባለድርሻ አካላት የተቀናጀ አሰራር እንዲከተሉ የሚያግዝ ማስፈጸሚያ ዝርዝር መመሪያ በማዘጋጀት ስለ አፈጻጸሙ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
2) በግል ተመዝጋቢዎችም ሆነ ለመኖሪያ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ቤት ግንባታ የሚውሉ በቂ የመሬት፣ የመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ ስታንዳርድ ዲዛይኖችን አዘጋጅቶ የማቅረብ ወይም በማህበራቱ በራሳቸው ተዘጋጅተው የቀረቡትን ዲዛይኖችን የማጸደቅና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ በተቀናጀ አግባብና በጸደቀው የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ስትራቴጂ መሰረት መፈጸማቸውን ይከታተላል፣ ይደግፋል፡፡
3) ከፌደራል ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሐረር ከተማ ደረጃ እና የተለያዩ ለመሬት አጠቃቀም የሚሆኑ የግንባታ ዲዛይኖችን በማዘጋጀት በክልሉ እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡
4) ከፌደራል ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ቤቶች ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ ድረስ ያለውን የግንባታ ሂደት የሚከታተል/የሚመራ አደረጃጀት በማዘጋጀት በክልሉ እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡





የሐረሪ ህዝብ ... ክልላዊ መንግስት
የ... ማህበር
አገልግሎት ክፍል
ጽ/ቤት

## 12. የሐረሪ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

### 1) ከሚሲዮኖች ጋር ቅንጅት በመፍጠር

ሀ) በግል ተመዝጋቢዎችና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ለተደራጁ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ማስፈጸሚያ በተዘጋጁ መመሪያዎች ላይ በተለያዩ አገሮች ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አባላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራት፣

ለ) በግል ተመዝጋቢዎችና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም መመሪያው ላይ የተቀመጠውን የምዝገባ ቀናት፣ የምዝገባ ቦታና ተመዝጋዎች የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች እንዲያሟሉ በግልጽ የማስገንዘብ ስራ መስራት፣ አደረጃጀታቸውን በአግባቡ ማጠናቀቅ፤

ሐ) በግል ተመዝጋቢዎችና ለመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም ተመዝጋቢዎች እንዲሞሉ በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተላኩ ቅጾችን በበቂ ሁኔታ በማዘጋጀት ማስሞላት፣

መ) በግል ተመዝጋቢዎችና በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም የተመዘገቡትን የአባላት ዝርዝር እንዲሁም የተሞሉ ቅጾችንና ሌሎች ተፈላጊ መረጃዎችን እና አባላትን በጥንቃቄ በማደራጀት በዲፕሎማቲክ ፓውች በወቅቱ ለውጭ ጉዳይ ሚ/ር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እንዲደርስ ማድረግ፣

ሠ) ስለ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር አደረጃጀትና አሰራር ከሚመለከተው የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል የሚላኩትን የተለያዩ ሰነዶች፣ ቅጾችና ውሎች በተገቢው መንገድ ለተጠቃሚዎች መድረሳቸውን ማረጋገጥ፣

ረ) ቅሬታዎች፣ ጥያቄዎች እንዲሁም ማብራሪያ የሚያስፈልጉ ጉዳዮች ካጋጠሙ በወቅቱ ለፌደራል ዳያስፖራ ተሳትፎ ጉ/ዳ/ጄ ለዋናው መ/ቤት ማቅረብ፣

ሰ) በግል ተመዝጋቢዎችን በተመለከተ መደራጀት ባይጠበቅባቸውም ሚሲዮኑ ለአፈጻጸም አመች እንዲሆን ተመዝጋቢዎቹን በቡድን በመለየት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳ/ጄኔራል በሽኚ ደብዳቤ የቡድኑን አባላት ዝርዝር በማካተት መላክ፣

ሸ) በግል ተመዝጋቢዎችና የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ፕሮግራም የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ በጸደቀው መመሪያ መሠረት ብቻ መፈጸሙን ማረጋገጥ፣

ቀ) በእያንዳንዱ አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የተሞሉ የአባላት ቅጾች፣ የተደራጁበት የመተዳደሪያ ደንብ፣ የአመራር አባላትን የመረጡበት የተፈረመ ቃለ ጉባኤ፣ የፈለጉትን የቤት አይነት ከሚሲዮኑ የመሸኛ ደብዳቤ ጋር መላክ፣

በ) የተመዝጋቢዎች አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባላት ከ12 ያላነሡ መሆኑን በማረጋጋጥ ሚሲዮኑ ሞዴል የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራትን መተዳደሪያ ደንብ በማቅረብ እንዲሞሉት በቃለ ጉባዔም የተደገፈ የአመራር አባላት መምረጥና ተፈራርሞ መላክ፣

ተ) በክልሉ በዚህ ፕሮግራም አፈጻጸምና ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ባለ የስራ ግንኙነት እንደ ድልድይ በመሆን ያገለግላል፣

### 2) በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ጋር ቅንጅት በመፍጠር

ሀ) አስፈላጊ መመሪያዎችን፣ ማንዋሎችን፣ ቅጾችን፣ ወዘተ... በወቅቱ ለሚሲዮኖች መላክ፤

ለ) ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር በወቅቱ ለሚሲዮኖች እንዲደርሱ ማድረግ፣

ሐ) ከሚሲዮኖች የሚላኩ የተሞሉ ቅጾችንና የማህበራት መመስረቻ ቃለ ጉባዔ፣ መተዳደሪያ ደንብና ሌሎች መረጃዎችን ለሚመለከታቸው የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት መላክና ስለጉዳዩ ክትትል ማድረግ፣

መ) የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራትን የምዝገባ ዕውቅና የሚገልጽ ደብዳቤ ከሚመለከታቸው የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት ሲላክ ለሚሲዮኖች ማስተላለፍ፣

ሠ) ከሚሲዮኖች፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ከሚመለከተው የቁጠባ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ እና ከሚመለከታቸው የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ የሥራ ክፍሎች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን በተመለከተ መከታተልና መረጃ መያዝ፣

ረ) ሚሲዮኑ በላካቸው የግል ተመዝጋቢዎች ዝርዝር መሠረት የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ማድረግ፣

ሰ) የግል ተመዝጋቢዎችን በተመለከተ ከመዘገባቸው በፊት የpull አካውንት በእያንዳንዱ ማኅበር ስም እየተመዘገበ እንዲከፈት ያደርጋል፣

ሸ) የግል ተመዝጋቢዎችን በማኅበር እያደራጀ ከአስፈላጊ መረጃዎች ጋር ለምዝገባ ለማኅበራት ማደራጃ ይልካል፣

ቀ) ተመላሽ ዳያስፖራ አባላትን በተመለከተ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መሥፈርቶች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባ የብቁነት ማስረጃ ይሰጣል፡፡

1. የተመላሽ ዳያስፖራው የጸና የፖስፖርት ቅጂ፣
2. ተመላሽ ዳያስፖራው የሌላ አገር ዜግነት ያገኙ ከሆነ የጸና የኢትዮጵያ ተወላጅነት መታወቂያ ካርድ ቅጂ፣
3. የጋብቻ ማስረጃ ዋናውንና ቅጂውን
4. የተመላሽ ዳያስፖራው ሁለት ፖስፖርት መጠን ፎቶ ግራፍ፣
5. ለዚህ ጉዳይ የተዘጋጀ የምዝገባ ቅጽና ውል በወካዩ ሥም ሞልቶና ፈርሞ ማቅረብ፣
6. በመረጡት የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ በውጭ ምንዛሪ ከፍለው በአገር ውስጥ በተከፈተው የብር አካውንት ገቢ ያደረጉበትን የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

3) **በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሰው ሀብት ማኔጅመንት ዳ/ጄኔራል ጋር ቅንጅት በመፍጠር**

ሀ) በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው እያገለገሉ የሚገኙ ዲፕሎማቶች እና ሎካል ሠራተኞች በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የምዝገባ ቅጽ፣የተደራጁበትን የመተዳደሪያ ደንብ፣ የአመራር አባላት የመረጡበትን የተፈረመ ቃለ ጉባኤ፣ የፈለጉትን የመኖሪያ ቤት ዓይነት እና የሚሲዮኑን ሽኚ ደብዳቤ ለሚመለከታቸው የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት ያስተላልፋል፡፡

ለ) በመኖሪያ የህብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁ በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው እያገለገሉ የሚገኙ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች ምዝገባ በቅርበት በመሥራት ተከታትሎ ያስፈጽማል፣ ተፈላጊውን መረጃ ለዲፕሎማቱና ለሎካል ሠራተኛው በሚሲዮኖች አማካኝነት ያሳውቃል፡፡

ሐ) አካውንት የሚከፈትላቸውን ዲፕሎማቶችና ሎካል ሠራተኞች አባላት ዝርዝር ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስተላልፋል፡፡

## 13. ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ሐረር

በክልሉ ከባንክ ዲፖዚትና ምዝገባ ጋር በተያያዘ ከሁለት አማራጮች ደንበኛው በሚፈልገው አገልግሎትና አማራጭ ሊጠቀም ይችላል፦

**አማራጭ-1 በግል ተደራጅተው ለምዝገባ የሚቀርቡ ቤት ፈላጊዎች**

1) ከአሁን ቀደም የቤቶች ል/መ/ኮ/ኤጀንሲ ይከተለው በነበረው የግለሰቦች የቤት ሂሳብ አከፋፈል መሰረት ለዚሁ ፕሮግራም የሚያገለግል በኢንተርፕራይዙ የሚተዳደር ብሎክ አካውንት ይከፈታል፣ አሊያም በቀድሞው የቤቶች ል/መ/ኮ/ኤጀንሲ አካውንት ሊተዳደር ይችላል።

**አማራጭ-2 በማህበር ተደራጅተው ለምዝገባ የሚቀርቡ ቤት ፈላጊዎች**

1) በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በግልም ሆነ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው ለምዝገባ የሚቀርቡ ቤት ፈላጊዎች እንደአግባቡ ከሐረሪ ዲያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና ከክልሉ ህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት በሚደርሰው ዝርዝር መሠረት ሂሳብ ይከፍታል፣
2) በማህበሩ ስም የተከፈተው የሂሳብ እንቅስቃሴ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብና በውሉ መሰረት እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል።
2) በግል ተመዝጋቢዎች የሚከፈት የባንክ ሂሳብን በተመለከተ ለሐረሪ ዲያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት መረጃ ያስተላልፋል፡
3) እንዲሁም ከሐረሪ ዲያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለተደራጁ ማኅበራት ገንዘብ ማስተላለፊያ የሚያገለግል የpull አካውንት ይከፍታል።
4) በተመሳሳይ በከተማ ልማት ቢሮ በሚቀርበው ጥያቄ መሠረት በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለተደራጁ ማኅበራት ገንዘብ ማስተላለፊያ የሚያገለግል አካውንት ይከፍታል።

## 14. የክልሉ ማህበራት ማደራጃና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት

1) በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን እና ተመላሽ ዳያስፖራ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው ለመመዝገብ የሚያስፈልጋቸውን የአደረጃጀት መመሪያዎችንና ቅጾችን ያሳውቃል፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ለሐረሪ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንደአስፈላጊነቱ ውክልና በመስጠት እንዲደራጁ ያደርጋል።
2) በውጭ ለሚኖሩ በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አማካኝነት ለመደራጀት የሚያስፈልጋቸውን ዝርዝር መመሪያና ሞዴል ቅጾች በማዘጋጀት በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም በሐረሪ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በኩል እንዲደርሳቸው ያደርጋል።
3) ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ለመጠቀም በውጭ የተደራጁ (ካሉ) ነባርና አዲስ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ከሐረሪ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ና ከንግድ ባንክ ጋር በመተባበር የቁጠባ ሂሳብ እንዲከፈትላቸው ያደርጋል፣ የመኖሪያ ቤቱን የግንባታ ክፍያ 50 ፐርሰንት ያሟሉና ሌሎች ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባ እውቅና ሰርቲፊኬት (ማስረጃ) እንዲያገኙ ያደርጋል።
4) የተመዘገቡና ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟሉ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የቦታ ዝግጅትና ግንባታ ፈቃድ እንዲያገኙ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ በማቅረብ እንዲፈቀድ ያደርጋል።
5) በውጭ የሚኖሩ ሆነው በምዝገባው ወቅት በአካል አገር ቤት የሚገኙ የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባላትን በተመለከተ በውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ከፍተው በአካል ቀርበው እንዲመዘገቡ ያደርጋል።

6) በኢፌዲሪ ሚሲዮኖች ተመድበው የሚያገለግሉ ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች በመኖሪያ ቤት ሕብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁ አባላት ዝርዝር መረጃ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከሐረሪ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት በተላከለት እና በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መረጃ መሠረት የግንባታውን ወጪ 50 በመቶ ያጠናቀቁ የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የምዝገባ እውቅና ሰርቲፊኬት እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

7) በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ዲፕሎማቶችና ሎካል ሰራተኞች ምዝገባ የፈጸሙባቸውን ቅጾች፣ የመተዳደሪያ ደንቦች፣ የአመራር ምርጫ ቃለ ጉባኤና ሌሎች መረጃዎችን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ከሐረሪ ዳያስፖራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ይረከባል፣ ያደራጃል፡፡

8) የቤቶች ግንባታ በውሉ መሠረት ሲጠናቀቅ ለማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ያስረክባል፡፡

9) ቤቶቹ ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ ድረስ ያለውን የግንባታ ሂደት የሚከታተል/የሚመራ አደረጃጀት ይፈጥራል፡፡

## 15. የሐረሪ ቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ

1) በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበር ተደራጅተውና እውቅና ተሰጥቷቸው ከሚመለከተው አደራጅ አካል በሚቀርበው ዝርዝር ዝግጅት የግንባታ የውል ስምምነት ይፈጽማል፤ በየደረጃው ግንባታቸው እንዲከናወን ያደርጋል፤ ግንባታቸው የተጠናቀቀውን ቤቶች ለሚመለከተው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማደራጃ ያስረክባል፣

2) ለግንባታ የሚያስፈልገው በዝግ አካውንት የተቀመጠውን የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ገንዘብ ግንባታውን ለማስጀመር የሚያስፈልገውን እንዲሁም የግንባታ ሥራውን በየደረጃው ለማከናወንና ለማጠናቀቅ የሚያስችለውን ፋይናንስ በየጊዜው በሚቀርብ የግንባታ አፈጻጸም መሠረት ደረጃ በደረጃ እየታየ እንዲለቀቅለት ይጠይቃል፣

3) የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ በተረከቡት መሬት ላይ በአግባቡና በዲዛይኑ መሠረት የሥራ ተቋራጮችን፣ አማካሪዎችንና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በማሳተፍ የቤቶችን ግንባታ በተቀመጠው ስታንዳርድና ውል መሠረት በማከናወን ለህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት ያስረክባል፡፡

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ጉዳዮች

## 16. ስለውክልና

1) ማንኛውም በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የመኖሪያ ቤት ፈላጊ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኃላ ሌሎች ከኀባታ በኃላ ያሉ ጉዳዮችን ለመከታተል በአካል መቅረብ ካልቻለ ተወካይ መወከል ይችላል፡፡ ሆኖም ግን አንድ ተወካይ ከሶስት አባል በላይ ውክልና ሊወስድ አይችልም፡፡

2) ተወካዩ የማህበር አባልም ሆነ የግለሰብ ተመዝጋቢውን ወክሎ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በዚህ ማስፈጸሚያ መመሪያ የተደነገጉትን ጉዳዮች አክብሮ የመስራት ኃላፊነት አለበት፡፡

3) ተወካዩ የተሳሳቱ መረጃዎችን በማቅረብ ወካዩ ተጠቃሚ እንዲሆን ካደረገ እንደ ያልተገባ ጥቅም ተጋሪ ተቆጥሮ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 17. የምዝገባ ጊዜ

የግል ተመዝጋቢዎችና መኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር የመኖሪያ የቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ይህ መመሪያ ከጸደቀ በኂላ በሚመለከተው ተቋም በሐረሪ ጋዜጣ ወይም በሌሎች መገናኛ አውታሮች በክልሉ ይፋ

፡፡

ከሚሆንበት ጊዜ ጀምሮ ምዝገባው የሚካኤድ ሲሆን የሚጠናቀቅበት ጊዜ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ቢሮ ወደፊት የሚገለጽ ይሆናል፡፡

## 18. የሂሳብ እንቅስቃሴና የገንዘብ ዝውውር ሁኔታ

1) የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት የሂሳብ እንቅስቃሴ ሁኔታ በመተዳደሪያ ደንቡና ለመኖሪያ ቤት በዝግ ሂሳብ የተቀመጠ ገንዘብ ማህበራት ማደራጃና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት በተወካይ የሥራ አመራር ወይም በዋና የሥራ አመራር አማካኝነት እንዲንቀሳቀስ ሲፈቅድና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሲጽፍ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡
2) በግል ተመዝጋቢዎች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አማካይነት ከሚከፈትላቸው የግል አካውንት ላይ ወደ ተደራጁበት ማኅበር ሂሳብ እንዲዘዋወር ከማህበራት ማደራጃና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በሚደርሰው ትዕዛዝ መሠረት ይህንኑ በመፈጸም ለማኅበራት ማደራጃ ያሳውቃል፡፡

## 19. የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ክትትል

1) በመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ተደራጅተው የተመዘገቡ አባላት የቤቶች ግንባታ የክልሉ መንግስት ባቋቋመው የቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ/ተቋም አማካኝነት ይሆናል፡፡
2) በተመሳሳይ በግል ተመዝግበው በመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ቤት ለመስራት የሚፈልጉ አባላት የክልሉ መንግስት በቤቶች ልማት ኢንተርፕራይዝ/ተቋም አማካኝነት እንዲገነቡ ያደርጋል፡፡
3) የግንባታውን ሂደት፣ የክፍያ አለቃቀቅ እና የጥራት ቁጥጥር ሥርዓት የሚደግፍ አደረጃጀት ይፈጠራል፣ ይህንን መመሪያ ተከትሎ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ይዘጋጃል፡፡
4) ቤቶቹ ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ ድረስ ያለውን የግንባታ ሂደት የሚከታተለው ከማህበራት ማደራጃና ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ይሆናል፡፡
5) በማህበር የሚገነቡ መኖሪያ ቤቶች ከርክክብ በፊት የግንባታ አፈጻጸማቸው መቶ ፐርሰንት የተጠናቀቁ ይሆናሉ፡፡

## 20. የመኖሪያ ቤት ርክክብና ቅድሚያ አወሳሰን

1) ከዚህ በፊት በማህበር ተደራጅተው የነበሩ በውጭ ሀገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በድጋሚ በዚህ መመሪያ መስፈርቱን አሟልተው ከተመዘገቡ ከአዲስ ተመዝጋቢ ማህበራት ቅድሚያ መብት ይኖራቸዋል፡፡
2) በማህበር የተደራጁ አባላት የመኖሪያ ቤት ርክክብን በተመለከተ ማህበሩ ግንባታውን ከሚያከናውነው አካል ጋር በገቡት ስምምነት መሠረት የሚፈጸም ሲሆን ለእያንዳንዱ የማህበር አባል የቤት ርክክብ የሚፈጸመው ግን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አሊያም በሐረሪ ቤቶች ልማት ኢንተርኘራይዝ/ተቋም ርክክብ መስፈርት አማካኝነት ይሆናል፡፡
3) በግል የተመዘገቡ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎችን በተመለከተ የቤት ግንባታ የሚካሄድላቸው በጋራ ሲሆን የመረጡትን ቤት መሠረት በማድረግ በዕጣ እንዲከፋፈሉ ይደረጋል፡፡
4) የመጀመሪያውን ፎርማሊቲ አሟልተው 50 በመቶ ክፍያ ያጠናቀቁና እውቅና ያገኙ ማህበራት ቁጥር ለግንባታ ከተዘጋጀው መሬት በላይ ከሆነ የቦታ አሰጣጡ የማኅበራቱ ተወካዮች በተገኙበት በዕጣ እንዲወሰን ይደረጋል፣

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሠረት በዕጣ መሬት የደረሳቸው ማኀበራት መሬቱ በተለያዩ የከተማው አካባቢዎች የሚገኝ ከሆነ ምርጫቸው በዕጣ የሚወሰን ይሆናል፣

## 21. ከፕሮግራሙ ስለመሰረዝ

1) በግል ተመዝጋቢዎችም ሆነ በማህበር የተደራጁ ተመዝጋቢው የምዝገባ መመሪያውን መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ እንደሆነ ከምዝገባ ፕሮግራሙ ከመሰረዙ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው ቢኖርም ከማህበሩ አባላት ውስጥ አንዱ ወይም የተወሰኑት አባላት መስፈርቶችን የማያሟሉ ከሆነ በግል ተጠያቂ ሆነው ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሚቀጥል ይሆናል፡፡

## 22. ቁጠባው ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ

በግል ተመዝጋቢዎችም ሆነ ከመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበራት መኖሪያ ቤት ፈላጊዎች ምዝገባ ተሰርዞ ገንዘቡ እንዲመለስ የተወሰነ ተጠቃሚ ግለሰብ ወይም ማህበር የሚመለሰው ገንዘብ በወቅቱ ምንዛሪ በኢትዮጵያ ብር ነው፡፡

## 23. ክልከላ

1) የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበራት የአደረጃጀት መመሪያ ላይ የተቀመጡ ክልከላዎች በሙሉ በዚህ ማስፈጸሚያ መመሪያ ተፈጻሚነት አላቸው፡፡

2) የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበር የአደረጃጀት መመሪያ ላይ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሚመለከት ከተቀመጠው መስፈርት ውጭ መመዝገብም ሆነ እንዲመዘገብ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## 24. ቅጣት

በዚህ ማስፈጸሚያ መመሪያ የተቀመጡትን የምዝገባ መስፈርቶች ሳያሟላ የተመዘገበ እና ክልከላዎችን የተላለፈ፣ ለመመዝገብ የሞከረ ወይም ሀሰተኛ መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ ማንኛውም ተመዝጋቢም ሆነ የተመዝጋቢ ተወካይ አግባብ ባለው የወንጀለኛ እና የፍትሐ ብሔር ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 25. የማስፈጸሚያ መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን ማስፈጸሚያ መመሪያ ማሻሻል ሲያስፈልግ መመሪያውን ያወጣው አካል ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## 26. ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህን መመሪያ ----------------------------- ቀን--------------ዓ.ም. ጀምሮ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

ሙራድ አብዱልሓዲ
የሀረሪ ህዝብ ክልል ፕሬዝዳንት
የካቲት/2007 ዓ.ም.
ሐረር

ቅጽ 007

ፎቶ

<u>አባሪ አንድ</u>

**በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና ተመላሽ የዳያስፖራ አባላት በአፓርትመንት እና ታውን ሀውስ በግል የመኖሪያ ቤት ልማት ፕሮግራም ላይ ለመመዝገብ የቤት ፍላጎት መግለጫ ቅጽ**

1. የአመልካች ሁኔታ፣

1.1. ስም -------------------- የአባት ስም --------------------የአያት ስም ----------------------

ፆታ --------------- ዕድሜ------------------- ብሔር---------------------------

ዜግነት---------------------- የፓስፖርት ቁጥር--------------------------------

1.2 የአመልካች እናት ስም ------------------------ የእናት አባት ስም ------------------------------

የእናት አያት ስም -------------------------------------

1.3 የመኖሪያ አድራሻ

- አገር------------------------------------ከተማ------------------------------------
- ፖ.ሳ.ቁ.--------------------------------- ፋክስ ቁጥር---------------------------
- ስልክ ቁጥር-------------------------------ኢሜል -----------------------------

1.4 የትዳር ሁኔታ

ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐

1.5 ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም------------------የአባት ስም------------------- የአያት ስም ---------------------

2. የሚፈልጉት የቤት አይነት

2.1. አፓርትመንት/ የጋራ ህንጻ (ፎቅ) ከሆነ ፤

ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

2.2 ታውን ሀውስ ከሆነ፡

ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

2.3 ታውን ሀውስ የክልሉ ባህላዊ ኪነ ህንጻ ቀመስ ከሆነ፡

ባለ 3 መኝታ☐ ባለ 4 መኝታ☐ ባለ 5 መኝታ☐ ባለ 6 መኝታ☐ ባለ 7 መኝታ☐

3. የገቢ ሁኔታ

3.1. የአመልካች ወርሃዊ የገቢ መጠን በብር ---------------------------- ምንጭ --------------------

3.2. የትዳር ጓደኛ የገቢ መጠን በብር ------------------------ ምንጭ -------------------------------

3.3. ጠቅላላ የገቢ መጠን በአኃዝ ------------- /በፊደል------------------------------------

4. **የተወካይ መረጃ፤**

4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት-------------------------------------------------------------------

4.2. የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-

- ክልል----------------------------ከተማ--------------------------------------
- ዞን/ክ/ከተማ--------------------------------ወረዳ ----------------------------
- ቀበሌ ----------------------------የቤት ቁጥር ------------------------------
- የቤት ስልክ ቁጥር --------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር ------------------------

5. ለምዝገባ የሚያስፈልግ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያስቀመጠው ገንዘብ

5.1 በቅድሚያ በልዩ ዝግ ሂሳብ ያስቀመጠው ዝቅተኛ መጠን ብር በአኃዝ -------------------

/በፊደል---------------------------------------------------------------------------------------------------/

5.2 የዝግ ሂሳብ የቁጠባ ደብተር ቁጥር ------------------------------------ ቅርንጫፍ -----------------------

6. ሂሳብ የሚከፍትበትና የቤቱን ዋጋ ክፍያ የሚፈጸምበት አማራጭ መንገድ፡-

6.1. የክፍያ አፈጻጸም በአንድ ጊዜ (100%)☐ በሁለት ጊዜ (50%)☐ ቅድመ ክፍያ (30%)☐ ቅድመ ክፍያ (ከ30% በላይ)______

7. እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

7.1 ቀደም ሲል በቤቶች ልማትና መ/ኮ/ኤጀንሲ በተዘረጉት የዳያስፖራ ቤት ልማት ፕሮግራም ያልተመዘገብኩና ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፣

7.2 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 30 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ማስቀመጤን፣ ቀሪውን 20 በመቶ ግንባታው 50% ሲደርስ የማስቀምጥና ግንባታው እንደተጠናቀቀ በሚመለከተው ተቋም ሲገለጽ ቀሪውን 50% የምከፍል መሆኑን፣

7.3 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

7.4 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረክብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፣

7.5 ወደፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም፣

7.6 ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአመልካች ሙሉ ስም-------------------------------------

ፊርማ --------------------------------

ቀን ----------------------------------

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ በግል ተመዝጋቢዎች ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው፡፡

ቅጽ 005

<u>አባሪ ሁለት</u>

ፎቶ

**በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም ተመላሽ ዳያስፖራ አባላት በመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበራት ለማደራጀት የአባልነት ማመልከቻ ቅጽ**

1. የህብረት ስራ ማህበሩ መጠሪያ ------------------------------------------------------------ የመኖሪያ ቤት ኃ/የተ/የህብረት ስራ ማህበር
2. የአመልካች ሁኔታ፤

   2.1.ስም --------------- የአባት ስም ----------------የአያት ስም ---------------------

   ፆታ -------- ዕድሜ---------- ብሔር-------------- ዜግነት--------------- የፓስፖርት ቁጥር------------

   2.2 የአመልካች እናት ስም ----------------------- የእናት አባት ስም -----------------------------

   የእናት አያት ስም-----------------------------------

   2.3. የመኖሪያ አድራሻ

   2.3.1 አገር-----------------------------------

   2.3.2 ከተማ-----------------------------------

   2.4 የትዳር ሁኔታ

   ያገባ/ች ☐ ያላገባ/ች ☐ በፍቺ የተለየ/ች ☐ በሞት የተለየ/ች ☐

   2.5.ያገባ/ች ከሆነ የትዳር ጓደኛ ስም ----------------የአባት ስም-----------------የአያት ስም------------------
3. የሚፈልጉት የቤት አይነትና የክፍል ብዛት

   3.1 አፓርትመንት/ የጋራ ህንጻ (ፎቅ)ከሆነ፤

   ባለ 2 መኝታ ☐ ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

   3.2 ታውን ሀውስ ከሆነ፡

   ባለ 3 መኝታ ☐ ባለ 4 መኝታ ☐

   3.3 ታውን ሀውስ የክልሉ ባህላዊ ኪነ ህንጻ ቀመስ ከሆነ፡

   ባለ 3 መኝታ☐ ባለ 4 መኝታ☐ ባለ 5 መኝታ☐ ባለ 6 መኝታ☐ ባለ 7 መኝታ☐
4. የተወካይ መረጃ፤

   4.1 የተወካዩ ስም ከነአያት-------------------------------------------------------------

   4.2 የተወካዩ የመኖሪያ አድራሻ ፡-

   - ክልል--------------------------ከተማ------------------------------------
   - ዞን/ክ/ከተማ------------------------------ወረዳ ---------------------------
   - ቀበሌ --------------------------የቤት ቁጥር ---------------------------

- የቤት ስልክ ቁጥር -------------------የሞባይል ስልክ ቁጥር -----------------------

5 እኔ ስሜ ከላይ የተገለጸው አመልካች

5.1 ቀደም ሲል በቤቶች ልማትና መ/ኮ/ኤጀንሲ በተዘረጋት የዳያስፖራ ቤት ልማት ፕሮግራም ያልተመዘገብኩና ተጠቃሚ ያልሆንኩኝ መሆኑን፣

5.2 ለምዝገባ ብቁ የሚያደርገኝ የቤቱን ግንባታ 30 ፐርሰንት በምዝገባ ወቅት በውጭ ምንዛሪ በዝግ ሂሳብ ያስቀመጥኩ መሆኑን እና ቀሪውን 20 በመቶ ግንባታው 50% ሲደርስ የማስቀምጥና ግንባታው እንደተጠናቀቀ በሚመለከተው ተቋም ሲገለጽ ቀሪውን 50% የምከፍል መሆኑን፣

5.3 በምረከበው ቤት በጋራ ህንፃ ህግ መሠረት ለመተዳደር ፈቃደኛ መሆኔን፣

5.4 በዚህ ማመልከቻ ቅጽ የሞላሁትና የሰጠሁት ማረጋገጫ ሀሰተኛ ሆኖ ቢገኝ የምዝገባው ውል የሚፈርስ መሆኑንና ቤቱን ለሚመለከተው ለማስረከብ ወይም በከፍተኛ የሊዝ ዋጋ ታስቦ ከነቅጣቱ ለመክፈል የምስማማ መሆኑን፣

5.5 ወደ ፊት የሚጠየቁ መረጃዎችን ለምሳሌ የጣት አሻራና ሌሎች መረጃዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ መሆኔን እንዲሁም

5.6 በተ.ቁ 1 ላይ በተገለጸው የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር ስም ከሌሎች የማህበሩ አባላት ጋር በፈቃደኝነት ለመደራጀትና የመኖሪያ ቤት ለመስራት የሚያስፈልገውን ቅድመ ሁኔታና መስፈርቶች በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ያማላሁ በመሆኑ የህብረት ስራ ማህበሩ በአባልነት እንዲቀበለኝና ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ተጠሪ የቤቱን ጉዳይ ተከታትለው እንዲያስፈጽሙ የወከልኳቸውና የሞላሁት መረጃ ሀሰት ሆኖ ቢገኝ በህጉ መሠረት ተጠያቂ እንደምሆን በመስማማት ይህን ቅጽ የሞላሁ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የህ/ስ/ማ/አባሉ ሙሉ ስም-----------------------------------

ፊርማ -------------------------------

ቀን ---------------------------------

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> ይህ ቅጽ በእያንዳንዱ የህ/ስ/ማህበሩ አባል ወይም ወኪል አማካኝነት ተሞልቶ የሚቀርብ ነው

አባሪ ሶስት

## የህንፃ ከፍታ፣ የአባላት ብዛት እና የቤት ዓይነት መግለጫ

I. አፓርትመንት (G+4 እና በላይ) አማራጭ የቤት ዓይነት ስብጥር እና የሚያስፈልግ የቦታ ስፋት (አዲስም ሆነ ነባር 12 አባላት)

| አማራጭ | የአባላት ብዛት | የቤት ዓይነት | በአንድ አፓርትመንት የሚኖር የቤቶች ብዛት ስብጥር | የሚያስፈልግ አማካይ የቦታ ስፋት በሜ/ካ | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ለአንድ ቤት | ጠቅላላ |
| 1 | 12 (1 ማኅበር) | ባለ 2 መኝታ ቤት | 3 | 80 | 240 |
| | | ባለ 3 መኝታ ቤት | 6 | 88 | 528 |
| | | ባለ 4 መኝታ ቤት | 3 | 96 | 288 |
| | | ለአንድ አፓርትመንት ጠቅላላ የሚያስፈልግ ቦታ ስፋት | | | 1056 |
| 2 | 12 (1 ማኅበር) | ባለ 3 መኝታ ቤት | 6 | 88 | 528 |
| | | ባለ 4መኝታ ቤት | 6 | 96 | 576 |
| | | ለአንድ አፓርትመንት ጠቅላላ የሚያስፈልግ ቦታ ስፋት | | | 1104 |
| 3 | 12 (1 ማኅበር) | ባለ 3መኝታ ቤት | 8 | 88 | 704 |
| | | ባለ 4መኝታ ቤት | 4 | 96 | 384 |
| | | ለአንድ አፓርትመንት ጠቅላላ የሚያስፈልግ ቦታ ስፋት | | | 1088 |

የግርጌ ማስታወሻ፡- 1) በግል የሚመዘገቡ ቤት ፈላጊዎች 12 በመሆን የሚኖሩበትን አገር መነሻ በማድረግ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

2) ከላይ የተመለከተው የቦታ ስፋት የከተማው አስተዳደር ባዘጋጀው የአባባቢ ልማት ኘላን ላይ ተመስርቶ የቦታ ስፋቱ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል፡፡

II- በታውን ሃውስ (G+1) የቤት አይነት የአባላት ብዛትና የሚያስፈልግ የቦታ ስፋት

| አማራጭ | የቤት ዓይነት | የአንድ ማኀበር የሚይዘው አባላት ብዛት | ለአንድ ቤት የሚሠጠው የቦታ ስፋት በሜ/ካ | የሚያስፈልግ አማካይ የቦታ ስፋት በሜ/ካ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ባለ 2 መኝታ ቤት | 12 | 120 | 1,440 |
| 2 | ባለ 3 መኝታ ቤት | 12 | 135 | 1,620 |
| 3 | ባለ 4 መኝታ ቤት | 12 | 150 | 1,800 |

የግርጌ ማስታወሻ፡- የማኀበር አባላት ከላይ ከተመለከቱት የመኝታ ቤት ምጣኔ በተለየ መንገድ መደራጀት ከፈለጉ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ለሚመርጡት የቤት ዓይነት ዲዛይን እራሳቸው እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡